AUTISM SPEAKS®

EARLY ACCESS TO CARE

# ህፃን ልጅዎ ከሚከተሉት ምልክቶች አንዱን ያሳያል/ታሳያለች ወይ?

- 12 ወራት ቢሆነውም/ቢሆናትም መኮላተፍም እንኳን የለም
- እስከ 12 ወራት ወደፊት ወደኋላ ምልክቶች - ማለት - ለማመልከት፣ ለማሳየት፣ ለመድረስ፣ ወይም እጅን ማወዛወዝ አለማሳየት
- 12 ወራት ቢሆነውም/ቢሆናትም በስም ሲጠሩ(ሯ)ት ምላሽ  አለመስጠት
- 24 ወራት ቢሆነውም/ቢሆናትም ምንም ቃል አለመናገር
- በማንኛውም እድሜ የመናገር፣ የመኮላተፍ ወይም የማህበራዊ ችሎታዎች መኳደል/መጥፋት
- ከእቃዎች ወይም ከመጫወቻ አካሎች ጋር ብዙ ግዜ ማሳለፍ
- ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎች ወይም ትግባሬዎች ድግግሞሽ

# ይህ ከሆነ፣ ምን ማድረግ አለብዎት?

**1** **ጊዜ አይውሰዱ። ድንገት ስጋት ካለዎት፣ ሀኪምዎን ያነጋግሩት። ልጅዎን ይበልጥ የሚያውቁት እርስዎ ነዎት።**

**2** **ከዚህ ገፅ በስተጀርባ ወይም መስመር ላይ የሚገኘውን የኦቲዝም ማጣርያ ቅፅ ይምሉትና ከሀኪምዎ ጋር በመሆን ድህረ እይታ ያድርጉበት።** ስለኦቲዝም ተጨማሪ መረጃዎች በዚህ ድር ጣቢያ ይገኛሉ፡- **www.AutismSpeaks.org/signs**

**3** **የህክምና ጣልቃ ገብነት ሂደት ወድያውኑ ጀምሩ።** ልጅዎ መደበኛ ምርመራ ባይሆንም ነፃ ግምገማ ማግኘት ይ ችላል። ልጅዎ ከ **36** ወራት በታች ከሆነ፣ የአካባቢዎን ከወሊድ እስከ ሶስት**(birth to three)** ወይም **early intervention** ፅ/ቤት ወድያው ስጋት ሲኖርዎት ይገናኙ። የአካባቢዎ ወኪል መረጃ ከዚህ በታችየሰፈረውነው፡-

**4** **እርዳታ ከፈለጉ ፡-** ለተጨማሪ መረጃ **www.AutismSpeaks.org** ይጎብኙ። የ**Autism Speaks (**ኦቲዝም ይናገራል**)** የኦቲዝም ምላሽ ቡድን **(autism response team)** ይገናኙ። ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ ነፃ መገልገያዎችንም ሊ ያቀርቡልዎት ይችላሉ። በእንግሊዝኛ፡- **888-AUTISM2 (888-288-4762)** • በስፓኒሽ፡- **888-772-9050** **familyservices@autismspeaks.org** • ቴክስት **“ART” to 30644**

## አሁኑኑ እርምጃ ይውሰዱ፡-በጥዋቱ ጣልቃ መግባት የሙሉ ህይወት ልዩነት ያመጣል።

Partially adapted from www.cdc.gov/actearly

AUTISM SPEAKS®
It's time to listen.

© 2013 Autism Speaks Inc. Autism Speaks and Autism Speaks It's Time To Listen & Design are trademarks owned by Autism Speaks Inc. All rights reserved. www.AutismSpeaks.org

# የተሻሻለው ኦቲዝም በህፃናት መቆጣጠርያ ዝርዝር (ኤም-ቻት)

ኤም-ቻት ከ16 እስከ 30 ወራት እድሜ ያላቸውን ህፃናት ለኦቲዝም አደጋ (autism spectrum disorders) (ASD) መጋለጣቸውን ለማጥራት ብቃቱ ተመስክሮለታል። AAP በ18 እና 24 ወራት መካከል ለሚገኙ ASD ምርመራ ጠቃሚነቱን ደግፏል። በhttp://www.mchatscreen.com የሚገኝ መመርያ በመጠቀም ጥያቄዎቹ ከ2 ደቂቃ ባነሰ ግዜ ሊከናወኑ ይችላሉ።
የሰለጠነ ባለሙያ በመልሶቹ ለመወያየትና ወደ ትክክለኛ መገልገያ ሊመራዎት ይችላል። 23ቱ ጥያቄዎች አንዳንዶቹን መልሶች በሚያብራራ በተከታይ ቃለ መጠይቅ መታጀብ ይኖርባቸዋል።

እባክዎን ስለልጅዎ **በአብዛኛው** የሚታየውን ገፅታ በሚከትሉት መልስዎን ይሙሉ። እባክዎ ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሱ። ስነምግባሩ ብርቅ ከሆነ (ለምሳሌ አንዴ ወይም ሁለት ግዜ ካዩት)፣ እባክዎ ልጅዎ እንዳላደረገ(ች)ው አድርገው ይመልሱ።

| | | (Yes) | (No) |
|---|---|---|---|
| 1. | ልጅዎን ዥዋዥዌ፣ በጉልበትዎ ላይ "ቁጭ-ብድግ"፣ ወዘተ. እያደረጉ ሲያጫውቱት ይደሰታል ወይ? | አዎን | አይደል |
| **2.** | **ልጅዎ ሌሎች ልጆችን ሲያይ ወደ እነርሱ ለመቅረብ ይፈልጋልን?** | **አዎን** | **አይደል** |
| 3. | ልጅዎ ደረጃዎች የመሳሰሉ መወጣጫዎችን ሲያይ ወደላይ መውጣት ይፍለጋል ወይ? | አዎን | አይደል |
| 4. | ልጅዎ ድብብቆሽ ጨዋታ መጫወት ደስ ይለዋልን? | አዎን | አይደል |
| 5. | ልጅዎ በስልክ የሚነጋገር፣ ወይም አሻንጉሊቶች የሚንከባከብ ወይም ሌላ ነገር አስመስሎ ያደርጋል ወይ? | አዎን | አይደል |
| 6. | ልጅዎ አንድን ነገር ፈልጎ ለመጠየቅ በጠቋሚ ጣቱ አመልክቶ ያውቃል ወይ? | አዎን | አይደል |
| **7.** | **ልጅዎ በአንድ ነገር ትኩረቱን ለማሳየት በጠቋሚ ጣቱ አመልክቶ ያውቃል ወይ?** | **አዎን** | **አይደል** |
| 8.......... ው | ልጅዎ በትናንሽ መጫወቻዎች (ለምሳሌ፡- መኪናዎች ወይም ጡቦች) በአፉ ሳይዳስስ፣ ሳያበላሻቸው፣ ሳይወረውራቸው በስነሥርአት ይጫወትባቸዋል ወይ? | አዎን | አይደል |
| **9.** | **ልጅዎ ለእርስዎ (ለወላጁ) አንዳንድ ነገሮችን ለማሳየት እቃዎችን ወደ እርስዎ ያመጣልን?** | **አዎን** | **አይደል** |
| 10. | ልጅዎ ከአንድ ወይም ከሁለት ሰኮንዶች ለበለጠ ጊዜ ትክ ብሎ አይን አይንዎን ይመለከታልን? | አዎን | አይደል |
| 11 | ከፍተኛ ድምጽ ልጅዎን በጣም የሚረብሸው ይመስላል? (ለምሳሌ ጆሮውን መድፈን) | አዎን | አይደል |
| 12. | ለልጅዎ ፈገግ ሲሉለት መልሶ ፈገግ ይላልን? | አዎን | አይደል |
| **13.** | **ልጅዎ እርሶ የሚያደርጉትን አይቶ ያንኑ ያደርጋልን? (ለምሳሌ ፊትዎን ቢያንጓጥጡ መልሶ ያንጓጥጣል?)** | **አዎን** | **አይደል** |
| **14.** | **ልጅዎ በስሙ ሲጠሩት ምላሽ ይሰጣልን?** | **አዎን** | **አይደል** |
| **15.** | **ባሉበት ክፍል ውስጥ ባሻገር ወደተቀመጠ መጫወቻ ቢያመለክቱ ልጅዎ ይመለከተዋል ወይ?** | **አዎን** | **አይደል** |
| 16. | ልጅዎ በእግሩ ይራመዳል? | አዎን | አይደል |
| 17. | ልጅዎ እርስዎ ወደሚያዩት ነገር ተከትሎ ያያል ወይ? | አዎን | አይደል |
| 18. | ልጅዎ ጣቶቹን ወደፊቱ ጠጋ አድርጎ ባልተለመደ ሁኔታ ያንቀሳቅሳቸዋልን? | አዎን | አይደል |
| 19. | ልጅዎ እያደረገ ያለውን ነገር እንዲያዩለት የእርስዎን ቀልብ ለመሳብ ይሞክራልን? | አዎን | አይደል |
| 20. | ልጅ "መስማት ተስኖታል" ብለው አስበው ወይንም ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉን? | አዎን | አይደል |
| 21. | ልጅዎ ሰዎች የሚናገሩት ነገር ይገባዋል ወይ? | አዎን | አይደል |
| 22. | ልጅዎ አንዳንድ ጊዜ የሌለ ነገር ትኩር ብሎ ያያልን? ወይም ያለ ምንም ዓላማ ወዲያና ወዲህ ይዟዟራል? | አዎን | አይደል |
| 23. | ልጅዎ ያልተለመደ ነገር ሲገጥመው የርስዎን ምላሽ ለማረጋገጥ ፊትዎን ይመለከታል ወይ? | አዎን | አይደል |

ለቁ. 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 8, 9, 10, 12, 13, 14, 15, 16, 17, 19, 21 ወይም 23 መልስዎ "አይደል" ከሆነ 1 ነጥብ ይስጡ፣ ወይም ለቁ. 11, 18, 20 እና 22 አዎን ከሆነ 1 ነጥብ ይስጡ። ጠቅላላ ነጥቦች 3 ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ልጅዎ ከሀኪምዎ ወይም ከጤና ባለሙያ ጋር ተከታይ ቃለ መጠይቅ (Follow-up Interview) ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል። ከቁ. 2, 7, 9, 13, 14, 15, ብቻ እንኳን ለሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ መልስዎ "አይደል" ከሆነ ሀኪምዎን ተከታይ ቃለ መጣአይቅ እንዲያደርግ ይጠይቁ። እነዚህ የኤም-ቻት ወሳኝ ጥያቄዎች ተብለው ይታሰባሉ። ምንም እንኳን ለጠቅላላው ውጤት ነጥቡ ከ3 በታች ቢሆንና ለወሳኞቹ ጥያቄዎችም ከ2 በታች ቢሆን፣ አሁንም ስጋት አለዎት፣ ጥያቄዎችዎንና ያለቀውን ፎርም ይዘው ለጥልቅ ግምገማ ወይም ለሌላ የህክምና በለሙያ እንዲመራ ለሃኪምዎ ይውሰዱ።

© 1999 Diana Robins, Deborah Fein, & Marianne Barton